# እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1-30/2017 የነበረው
# የአየር ጠባይ ግምገማ


ባለፈው የሴፕቴምበር ወር የነበረው የክረምት ዝናብ በመጠንም ሆነ በስርጭት ረገድ በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ያዳረሰ ሲሆን፣ ከሰሜን ምሥራቅና ከምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎችም በመደበኛ ሁኔታ ዝናቡ ከሚወጣበት ጊዜ በተወሰኑ ቀናት ዘግይቶ ተስተውሏል። በተጨማሪም በወሩ ውስጥ አልፎ አልፎ ከተፈጠረው ጠንካራ ዝናብ ሰጭ የደመና ሽፋን በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል። ከ50 ሚ.ሜ በላይ ሆነ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸው ስፍራዎች መካከል ለመጥቀስ በጊምቢ 107.1፣ 68.8 እና 64.9፣ በአይራ 79.5፣ በቡለን 68.2 እና 66.7፣ በዳንግላ 54.4 እና 50.9፣ በዲላ 52.7፣ በጎንደር 61.4፣ በኑራኢራ 52.0፣ በሽራሮ 55.5፣ በላሬ 53.1፣ በከማሺ 67.1፣ በሶጊ 80.1፣ በካራቆሬ 82.3፣ በማይፀምሪ 84.9፣ በነቀምቴ 72.0 በቋራ 65.7 እና 63.0፣ በጠርቻ 64.2፣ በሳውላ 64.2፣ ባህርዳር 52.4፣ በአቦቦ 55.0፣ በአዲስ አበባ ቦሌ 53.5፣ በሐዋሳ 55.0 እንዲሁም በአሮርሳ 52.6 በሚ.ሜ. ይገኙበታል።

በአጠቃላይ ባለፈው ወር በትግራይ፣ በአማራ፣ በአብዛኛው ኦሮሚያ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በደቡብ አፋር፣ በድሬዳዋ፣ በሐረሪ እና በሰሜን ሶማሌ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ አግኝተዋል።


ባለፈው ወር የነበረው ዝናብ ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ከትግራይ የምዕራብ ትግራይ፣ አማራ፣ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ አብዛኛው ኦሮሚያ፣ አዲሰ አበባ፣ ድሬዳዋና ሐረሪ እንዲሁም ሰሜን ሶማሌ ከ50-533 የሚደርስ ዝናብ ከ10-28 ቀናት ያህል ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 6 እና 7)፡፡

ባለፈው የሴፕቴምበር ወር ነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር ከትግራይ የምዕራብ ትግራይ፣ አማራ ከጥቂት ኪሰ ቦታ በስተቀር፣ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ ኦሮሚያ፣ አዲሰ አበባ፣ ድሬዳዋና ሐረሪ፣ ከሶማሌ የጅግጅጋ፣ የደገሀቡርና የቀብሪደሀር ዞኖች እንዲሁም ከአፋር የዞን 3 እና 5 አካባቢዎች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የዝናብ መጠን የነበራቸው ሲሆን፣ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸው (ካርታ 8)፡፡


ካርታ6   እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ7   እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2017 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ8 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1-30/2017 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻው ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፈው የሴፕቴምበር ወር የክረምት ዝናብ በመጠንም ሆነ በስርጭት ረገድ አብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ያዳረሰ ነበር፤ በሰሜን ምሥራቅና በምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎችም በመደበኛ ሁኔታ ዝናቡ ከሚወጣበት ጊዜ በተወሰኑ ቀናት መዘግይት ተስተውሏል። በተለያዩ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች በተለይም ትግራይ፣ አማራ፣ አፋር፣ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ ጋምቤላ፣ አብዛኛው ኦሮሚያ፣ አዲስ አበባ ፣ድሬዳዋ፣ ሐረሪ፣ ጅግጅጋና ሺንሌ ዞኖች በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተጠናከረና የተስፋፋ እርጥበት ነበራቸው፡፡ በመሆኑም ከላይ በተጠቀሱት አብዛኛዎቹ የመኸር ሰብል አምራች አካባቢዎች ላይ የተሻለ እርጥበት እንዲኖራቸው አስችሏል፡፡ ይህም ሁኔታ የአፈርን እርጥበት ከማሻሻል እንዲሁም ተክሎች የሚያስፈልጋቸውን ውኃ ከማቅረብ አንጻር ገንቢ ሚና ነበረው፡፡ እንድሁም በሀገሪቱ ልዩ ልዩ ክፍሎች በሚያዝያ ተዘርተው በአበባና ፍሬ በማፍራት ላይ ለሚገኙና የውሃ ፍላጎት ደረጃ ላይ ላሉ የረጅም ጊዜ ሰብሎች እንዲሁም በክረምቱ ወቅት ለተዘሩ ለብርዕና ለጥራጥሬ ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የዉሃ ፍላጎት መሟላት አዎንታዊ ገጽታ ነበረዉ። በአንፃሩም ዝናብ አጠር የሆኑ የሀገሪቱ ምሥራቃዊ አጋማሽ ላይ የሚገኙ ቦታዎች የተሻለ እርጥበት በማግኘታቸው ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት የተሻለ ጠቀሜታ እንደነበረዉ እሙን ነው፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ በነበረዉ ከባድ ዝናብ ዝናብ አጠር ለሆኑና ዉሃን የማቆር ሥራዎችን ለማከናወን፣ ለግጦሽ ሣር መሻሻልና ለመጠጥ ዉሃ አቅርቦት አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ቢሆንም፤ ከመስክ የደረሰን ሪፖሪት እንደሚያመለክተው በአንዳንድ በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ የተለያዩ ሰብሎች እና ቋሚ ተክሎች ላይ እንዲሁም በሰው ሕይወትና በንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል (ካርታ 9)፡፡

ባሳለፍነው የመስከረም ወር በአንዳንድ አካባቢወች ላይ ከፍተኛ ዝናብ ተከስቶ በሰዎችና በንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል፡፡

የደረሱን መረጃወች እንደሚያሳዩት ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸው መካከል፡-

<u>አማራ ክልል</u>

- ✓ በቀን 21/09/2010 በቡሬ ጣቢያ ላይ ከንፋስ ጋር ቀላቅሎ የጣለው ከባድ ዝናብ በሰብሎች ላይ ጉዳት አድርሷል፡፡
- ✓ በቀን 04/09/2010 በካራቆሬ ጣቢያ ከባድ ዝናብ ጥሎ አንድ መኖሪያ ቤት ከጥቅም ወጭ ሲያደርግ አስር ቤቶች ደግሞ በጎርፍ ተከበው ነበር፡፡
- ✓ በቀን 04/09/2010 በፓዊ የጣለው ዝናብ በቤቶችና በሰብሎች ላይ ጉዳት አድርሷል፡፡

- ✓ በቀን 04/09/2010 በመራዊ የጣለው ከባድ ዝናብ በመብራት ፖሎች ንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል፡፡

<u>አፋር ክልል</u>

- ✓ በቀን 01/09/2010 በኤሊዳር ጣቢያ የተመዘገበው ከባድ ዝናብ ከዝናቡ ጋር ተከትሎ በነበረው የመብረቅ አደጋ አንድ ሰው ሲሞት ሶስት ሰዎች ላይ ከባድ ጉዳት አድርሷል፡፡


<u>ደቡብ ክልል</u>

- ✓ በቀን 21/09/2010 ተርጫ ጣቢያ የተመዘገበው ከባድ ዝናብ በማሳዎች ላይ ወሃ በመተኛት የሰብሎች ጉዳት አስከትሏል፡፡

<u>ጋምቤላ ክልል</u>

በቀን 22/09/2010 ጋምቤላ ጣቢያ የተመዘገበው ከባድ ዝናብ በቤቶችና ንብረት ላይ ጉዳት አስከትሏል

ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2017 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር1-30/2017 የነበረው የአየር ጠባይ

## በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 1-30 ሴፕቴምበር 2017 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ የተሻለ የእርጥበት መጠን በምዕራብ፣ በመካከለኛውና በደቡባዊ የአገሪቱ አጋማሽ ተፋሰሶች ላይ ተስተውሏል$ በዚህ መሰረት ከፍተኛ እርጥበት የነበራቸው ተፋሰሶች አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ አብዛኛው ስምጥሸለቆ፣ የተከዜ ምእራባዊ አጋማሽ፣ የላይኛውና የመካከለኛው አዋሽ፣ የላይኛው ዋቢሸበሌና ገናሌዳዋ ተፋሰሶች ሲሆኑ፤ የመካከለኛው ዋቢሸበሌና የመካከለኛው ገናሌዳዋ፣ የተከዜ ምስራቃዊ ክፍል እንዲሁም የታችኛው አዋሽ ተፋሰሶች ደግሞ መጠነኛ እርጥበት የተሰተዋለባቸው ናቸው$ በሴፕቴምበር ወር በአብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ ከባድ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ ዝናቡ በመጠኑ ከፍተኛ በመሆኑ በእንዳንድ ተፋሰሶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ቢኖረውም ለዉሃ ሀብት ዘለቄታ አገልግሎት ጠቃሚ ገፅታ ይኖረዋል (ካርታ 10)፡፡

ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2017 ድረስ በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



## እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 1-31/ 2017 የሚኖረው

## የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ የክረምት ድንበር ወደ ደቡብ አቅጣጫ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በደቡብ የሀገሪቱ አጋማሽ ላይ እየተጠናከሩ ስለሚሄዱ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብ እና በደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ክፍሎች ላይ በተጠናከረ ሁኔታ ዝናብ የሚያገኙ ሲሆን፤ በተመሳሳይ ሁኔታም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ ዝናቡ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በአብዛኛው የሰሜን አጋማሽ የኢትዮጵያ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማ እና ነፋሻማ የአየር ጠባይ ጎልቶ ሊታይ እንደሚችልና ከዚሁ ጋር ተያይዞም የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ እንደሚስተዋል ይጠበቃል፡፡

በሚቀጥለው ወር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በምዕራብና በደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ እንደሚኖራቸውና አልፎ አልፎም ባሉት ቀናት ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ከባድ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በአጠቃላይ በመጪው ወር ከኦሮሚያ ክልል ጅማ<u>፣ ኢሉአባቦራ፣ ምዕራብ እና ምሥራቅ ወለጋ፣ አርሲና ባሌ፣ ምዕራብና ምሥራቅ ሐረርጌ፣ የቦረናና የጉጂ ዞኖች፣ ድሬዳዋና ሐረሪ፤ አዲስ አባባ፤ ጋምቤላ፤ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፤ ምዕራብ ትግራይ፤ ከአማራ ክልል የሰሜንና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ምዕራብ ጎጃም፣ ሰሜን ሸዋ እንዲሁም የባህር ዳር ዙሪያ እና አገው አዊ፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የወላይታ፣ የከፋና የቤንች ማጂ፣ የወላይታ እና የደቡብ ኦሞ፣ የጉራጌ፣ የሲዳማ፣ የጌዲዮ እና የሰገን ህዝቦች እንዲሁም ከሶማሌ ክልል ሁሉም ዞኖች በአብዛኛው ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ እና በጥቂት ሥፍራዎቻቸው ላይ ደግሞ ከመደበኛው በላይ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል</u>፡፡ <u>በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚፈጠሩ ጠንካራ ደመናዎች በሰሜንና በደቡብ ወሎ እንዲሁም በደቡብ አፋር ዞን 3 እና 5 አነስተኛ ዝናብ ይኖራል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች ደረቅ ሆነው ይቆያሉ፡፡</u>

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1-31/2017 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

## በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የኦክቶበር ወር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በምዕራብና በደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ እንደሚኖራቸውና እየተጠናከሩ እንደሚቀጥል ያመላክታሉ። ይኸም ሁኔታ ወቅታዊ ዝናብ ማግኘት በሚጀምሩት በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የአገሪቱ ክፍሎች አካባቢ ላይ የማሳ ዝግጅት ለማድረግና ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር

የሚጠበቅ ሲሆን፤ በአካባቢው ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት ጥሩ አስተዋጽዕ እንደሚኖረው ይገመታል። በተመሳሳይ ሁኔታም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ ዝናቡ ቀጣይነት የሚኖረው በመሆኑ ቀደም ብለው ለተዘሩና አልፎ አልፎ ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙ፣ ዘግይተው ለተዘሩና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ለመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በአካባቢው ለሚገኙ ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች፣ ለመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ለግጦሽ ሣር ልምላሜ የጎላ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። በተጨማሪም የሚጠበቀው ቀጣይነት ያለው የእርጥበት ሁኔታ በጎርፍ በተጠቁ አካባቢዎችና በድጋሚ ለተዘሩ ሰብሎች አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር እሙን ቢሆንም። አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ከባድ ዝናብ ሊኖራቸው እንደሚችል በትንበያው በተጠቀሱት አካባቢዎች አስቀድሞ ልዩ ትኩረትና ጥንቃቄ እንዲደረግ የሚመከር ሲሆን በተለይም የደረሱ ሰብሎች እንዳይበላሹ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድርግ ያስፈልጋል።

በተጨማሪም በአብዛኛው የሰሜን አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ ፀሐያማ እና ነፋሻማ የአየር ጠባይ ጎልቶ ሊታይ እንደሚችልና ይህም ሁኔታ  በተለይም በዚህ ጊዜ የሰብል ስብሰባቸውን በሚያካሂዱ በአንዳንድ የደጋውና የወይና ደጋ የአገሪቱ ክፍሎች ሰብል በደረሰባቸው አካባቢዎች ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባው አመቺ ሁኔታን የሚፈጥር ቢሆንም፤ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ እንደሚስተዋል በመጠበቁ በመደበኛ ሁኔታ በበጋ ወቅት ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በመከሰት ሣቢያ የሚፈጠር ውርጭ በአንዳንድ የመካከለኛው የሰሜንና የደቡብ ደጋማ የአገሪቱ ሥፍራዎች በሰብሎች ጤናማ እድገትና በእንሰሳት ጤና ላይ ጉዳት ሊያአስከትል ስለሚችል ተገቢው ክትትል መደረግ ይኖርበታል።

## <u>እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1-31/2017 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ</u>

የሚቀጥለው የኦክቶበር ወር የበጋው የመጀመሪያ ወር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በአብዛኛው የሰሜንና የሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ እርጥበቱ እየቀነሰ የሚሄድ ሲሆን፤ በሌላ በኩል የተራዘመ የክረምት ወቅት ዝናብ ያላቸው የምዕራብ አጋማሽና ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው የሆኑት የደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት የሚስተዋልበት ወር ነው$ በዚህ መሰረት በአብዛኛው ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ ገናሌዳዋና ስምጥሸለቆ፣ የአባይ ደቡባዊና ምዕራባዊ አጋማሽ ክፍል፣ የታችኛው ተከዜ፣ የታችኛውና የመካከለኛው አዋሽ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ዋቢሸበሌ እንዲሁም የኦጋዴን ተፋሰሶች መደበኛና በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ እንደሚያገኙ ትንበያው ይጠቁማል$ ይህም ሁኔታ በተለይ በደቡባዊ አጋማሽ በሚገኙ በታችኛው ተፋሰሶች ላይ ከላይ በሚመጣው የክረምት ዝናብ የወንዝ ፍሰትና የወቅት ዝናብ ጋር ተዳምሮ የጎርፍ ስጋት ሊያስከትል ስለሚችል ቅድመ ጥንቃቄ አስፈላጊ መሆኑን እንጠቁማለን።